# የዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን

## መመሪያ ቁጥር 134/2010

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
መጋቢት 2010 ዓ.ም

# የዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 134/2010

የንግድ ስምምነት ለማይመለከታቸው የገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥሪት አገር ለመወሰን፣ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል፣ ለሥሪት አገር ምልክቶች እና መለያዎች አጠቃቀም፣ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ፍትሀዊ ያልሆነ ውድድር እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ከለላ ለማድረግ፣ የገቢና ወጪ የንግድ ዕቃዎች ስታትስቲካዊ መረጃ ለመያዝ በማስፈለጉ፣

በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ወይም የእነዚህ ዕቃዎች ማሸጊያ የተሠሩበትን አገር የሚያስረዳ መግለጫ አሠራር የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባለሥልጣኑ የሥራ ክፍሎች እና ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የአስመጪዎችና ላኪዎች መብቶችና ግዴታዎችን በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 107 ንዑስ አንቀጽ (4) እንዲሁም በአንቀጽ 180 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "**የዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን መመሪያ ቁጥር** 134/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ከታች የተዘረዘሩት ቃላት የሚከተሉት ትርጓሜዎች ተሰጥቷቸዋል።

   1) "**የሥሪት ሀገር**" ማለት አንድ ዕቃ የተሰራበት፣ የተመረተበት፣ የበቀለበት ወይም የተገኘበት ሀገር ሲሆን የዕቃዎች የመጨረሻ መሰረታዊ የምርት ሥራ የተካሄደበትን ወይም የኢኮኖሚያዊ እሴት ጭማሪ የተደረገበትን አገር ይጨምራል።
   2) "**መሠረታዊ ለውጥ**" ማለት በተጣጣመ የሸቀጦች አሰያየም ሥርዓት የሸቀጦች አመዳደብ ደንብ መሠረት የመጨረሻው ምርት የታሪፍ አንቀፅ ከምርት ግብዓቱ የታሪፍ አንቀጽ የተለየ ሲሆን ነው።
   3) "**ልዩ የውጭ ገበያ ዕድል**" ማለት በኢኮኖሚያቸው የ... ...በማደግ ላይ ላሉትና

ወደኋላ ለቀሩት ሀገራት የውጭ ንግዳቸውን ለማበረታታት እንዲችሉ የሰጡት የኮታና ቀረጥ ነፃ የውጭ ንግድ ዕድል ነው፡፡

4) **"አምራች"** ማለት የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ጥሬ ዕቃ ተጠቅሞ ምርት በማምረት ወይም በጥሬ ዕቃ ደረጃ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነው፡፡

5) **"የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ"** ማለት ዕቃው የተሠራበትን ወይም በተፈጥሮ የተገኘበትን አገር የሚያመላክት ሲሆን ከሰርተፊኬቱ በተጨማሪ በዕቃው ወይም በዕቃው ማሸጊያ ላይ በግልጽ የተፃፈ መግለጫ ማለት ነው፡፡

6) **"የሥሪት አገር የምስክር ወረቀት"** ማለት አንድ ዕቃ ስለተመረተበት ወይም ሥለተገኘበት አገር ትክክለኛነት ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

7) **"ኢትዮጵያ ንግድ ስምምነት ካደረገችባቸው ሀገራት ውስጥ የተመረቱ ዕቃዎች"** ማለት ኢትዮጵያ ንግድ ስምምነት ባደረገችባቸው ሀገራት ስምምነቶች የተቀመጠውን የሥሪት ሀገር መስፈርት የሚያሟሉ ምርቶች ናቸው፡፡

8) **"ኢትዮጵያ ንግድ ስምምነት ያደረገችባቸው ሀገራት የሥሪት አገር አወሳሰን ፕሮቶኮል"** ማለት አንድ ዕቃ ኢትዮጵያ የነፃ ንግድ ስምምነት ባደረገችባቸው ሀገራት የተመረቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተዘጋጀ ደንብና አሰራር ማለት ነው፡፡

9) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

10) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላት እና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን፤</u>

ይህ መመሪያ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ገቢ ዕቃዎች እና ከአገር በሚወጡ ወጪ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን አይጨምርም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን</u>

4. <u>የንግድ ስምምነት የማይመለከታቸው ዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን መስፈርቶች</u>

1) አንድ ዕቃ በአንድ አገር ተመረተ ወይም ተሰራ የሚባለው ከሚከተሉት የሥሪት አገር መወሰኛ መስፈርቶች (origin criteria) አንዱን ሲያሟላ ነው፡፡

(ሀ) ዕቃው በአምራቹ አገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተመረተ ወይም የተገኘ ሲሆን፤

(ለ) ዕቃው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከሌላ አገር የመጡ የምርት ግብዓቶችን በመጠቀም

የተመረተ እና የምርት ሂደቱ በምርት ግብዓቶቹ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ከሆነ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ) ለተደነገገው አፈፃፀም ሲባል በአንድ አገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተመረቱ ወይም የተገኙ ተደርገው ይወሰዳሉ፤

(ሀ) ከአንድ አገር መሬት ወይም የባህር ወለል ተቆፍረው የወጡ ማዕድናት፣

(ለ) በአንድ አገር ውስጥ የተመረቱ የእርሻ ምርቶች፤

(ሐ) በአንድ አገር ውስጥ የተወለዱና ያደጉ እንስሳትና ተዋፅኦቻቸው፣

(መ) ከአደንና ከዓሳ ማስገር ሥራ የተገኙ የምርት ውጤቶች፤

(ሠ) ከአንድ አገር የባህር ክልል ውጪ የአገሩን መርከብ በመጠቀም ከዓሳ ማስገር እና ሌሎች ከባህር የተገኙ የምርት ውጤቶች፤

(ረ) ከላይ በፊደል ተራ "ሠ" የተጠቀሱትን የምርት ውጤቶች ብቻ እንደ ግብዓት በመጠቀም የተመረቱ ምርቶች፤

(ሰ) በአንድ አገር ውስጥ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩ አሮጌ ውዳቂ ዕቃዎች፣

(ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሰ" የተጠቀሱትን በመጠቀም በአንድ አገር የተመረተ ምርት፤

3) የዕቃው የሥሪት አገር ሲወሰን፣ ከዕቃው ጋር አብረው የሚሸጡ፣ ዓይነትና ብዛታቸው ለዕቃው መደበኛ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ አክሰሰሪዎች፣ መለዋወጫዎች፣ የዕጅ መሣሪያዎችና ስለዕቃው አጠቃቀም መመሪያ ወይም መረጃ የሚሰጡ ማቴሪያሎች ከዕቃው ጋር ተመሣሣይ የሥሪት አገር እንዳላቸው ተደርጎ ይወሰዳል።

4) ዕቃውን በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ ወይም ዕቃውን ሙሉ ለሙሉ አንድ ጊዜ ለማምረት የማይቻል በመሆኑ ምክንያት ዕቃው ሳይገጣጠም ወይም ተበታትኖ ከአንድ በላይ በሆነ ጭነት ወደ አገር እንዲገባ የተደረገ ከሆነ፣ ወይም በዕቃው አስመጪ ጥያቄ አንድ ዕቃ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

5) የዕቃው የሥሪት አገር ሲወሰን የዕቃው ማሸጊያና የማሸጊያ ማቴሪያል እና ኮንቴይነር ከግምት ውስጥ አይገቡም፤ ከያዙት ዕቃ ጋር ተመሳሳይ የሥሪት አገር እንዳላቸው ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም ለጉምሩክ ቀረጥ ሲባል ዕቃውና ማሸጊያው ተለያይተው የሚታዩ ከሆነ፣ የማሸጊያ ማቴሪያሉ የሥሪት አገር ተለይቶ ሊወሰን ይችላል።

6) ዕቃው በአለም አቀፍ ድርጅት ፈቃድ ስር የተመረተ ከሆነ ከላይ የተዘረዘሩትን የሥሪት አገር አወሳሰን ደንቦች የሚያሟላ እስከሆነ ድረስ የተመረተበት አገር የዕቃው የሥሪት አገር ይሆናል።

7) ወደ አገር ውስጥ የገባው ወይም የሚገባው ዕቃ የሥሪት አገር ከላይ በተዘረዘሩት የሥሪት አገር አወሳሰን ደንቦች መሰረት የተወሰነ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት የአስመጪው ይሆናል፡፡

5. <u>የዕቃዎች የሥሪት አገርን ለመወሰን ግምት ውስጥ የማይገቡ ሁኔታዎች</u>

1) የዕቃው የሥሪት አገር ሲወሰን፣ ዕቃውን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋሉ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ነዳጅ፣ የማምረቻ ህንፃና መሣሪያ፣ የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችን ጨምሮ፣ ማሽኖች እና የዕጅ መሣሪያዎች መጨረሻ ላይ የዕቃው አካል የማይሆኑ በመሆኑ የሥሪት አገር ለመወሰን ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

2) የሚከተሉት የሥራ ሂደቶች የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያስከትሉ ሆኑም አልሆኑም ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የሥሪት አገር ለመወሰን ከግምት ውስጥ አይገቡም፤

(ሀ) በምርት ማጓጓዝ ወይም ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት፤

(ለ) የዕቃዎችን የማጓጓዝ ሂደት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤

(ሐ)ዕቃዎችን ለማሸግ ወይም ለሽያጭ ለማዘጋጀት ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤

(መ)ዕቃዎችን በአየር የማናፈስ፣ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣የተበላሹ ክፍሎችን የመቀየር፣ ማለስለሻ የመቀባት ወይም ዝገት የማስወገድ፣ ተፍጥሮአዊ ሁኔታዎች በዕቃው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀለም የመቀባት፣ የማጠብ፣ የማጽዳት፣ የማበጠር፣ የመፈተግ፣ የመለየት፣ የመመዘን፣ የመሞከር፣ የመለካት፣ የማሸግ፣ እሽጎችን የመፍታትና መልሶ የማሸግ፣ የመከፋፈል፣ ምልክት የማድረግ፣ በውሃወይም በሌላ ፈሣሽ ነገር አያያዝ ማድረግ፣ በጨው የመንከር፣ የመላጥ፣ የመከካት፣ የመውቃት እና የእንስሳት እርድ የመሳሰሉ ቀላል ሂደቶች ክንውን፤

(ሠ) የተሟላ የምርት ውጤት ለማስገኘት የሚከናወን ቀላል የመገጣጠም ሥራ፤

(ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 5 የተዘረዘሩትን የሥራ ሂደቶች በማጣመር የሚከናወን ማንኛውም የሥራ ሂደት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለዕቃዎች የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

6. የንግድ ስምምነት የማይመለከታቸው የገቢ ዕቃዎች የሥሪት አገር ሠነድ ስለማጣራት እና ስለማረጋገጥ

1) ገቢ ዕቃዎች የሥሪት አገር ደንቦችን አሟልተው በአንድ አገር ውስጥ መመረታቸውን ለማረጋገጥ፣ አስመጪው በላኪው አገር ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ፣ የተፈረመ እና ማህተም የተደረገበት የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰነድ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፤

2) ባለሥልጣኑ ወደ አገር የገባው ዕቃ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ሲቀርብለት በዕቃው የሥሪት አገር ላይ ጥርጣሬ ካለው ከአስመጪው ወይም ከወኪሉ ድርጅት፣ ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል፤

3) ባለሥልጣኑ በዕቃው የሥሪት አገር ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጠው ድረስ አስፈላጊውን ዋስትና በመያዝ እንደ አግባብነቱ ናሙና በማስቀረት ዕቃውን መልቀቅ ይችላል፤

4) በሰርቲፊኬቱ ላይ የሚታዩ ጥቃቅን የጽህፈት ግድፈቶች ሰርቲፊኬቱን ዋጋ ላያሳጣው የሚችል ሲሆን ከሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች ጋር ተገናዝቦ እንዲወሰን ይደረጋል፡፡

7. ለጠረፍ ንግድ የሚያገለግል ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት

የጠረፍ ንግድን ለማሳደግ ከጎረቤት አገሮች ጋር በተደረሰ ስምምነት መሠረት ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲቀርብ የተወሰነ እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

1) ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርቲፊኬቱ ቅርበት ባለው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

2) በጠረፍ ንግድ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በጠረፍ ንግድ የተዘጋጀውን ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመሙላት ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በቅርብ ለሚገኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ማቅረብ አለበት፡፡

3) ከኢትዮጵያ ወደ ጎረቤት አገር የሚላኩ ዕቃዎች ከሆኑ በቅርብ የሚገኘው የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ዕቃዎቹ በጠረፍ ንግድ የዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ

የተካተቱ መሆናቸውን እና የሥሪት አገር መስፈረቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ በሠርተፊኬቱ ላይ ፊርማ እና ማህተም ማድረግ አለበት።

4) ከጉረቤት አገር ወደ ኢትዮጵያ በጠረፍ ንግድ ላይ በተደረሰ ስምምነት መሠረት ዕቃዎች ሲገቡ፣ በቅርብ የሚገኘው የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ በጠረፍ ንግድ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርተፊኬቱ ላይ የተዘረዘሩት ዕቃዎች በጠረፍ ንግድ የዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

5) ከጎረቤት አገሮች በሚመጣው የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ላይ የተፈረመው ፊርማ እና ማህተም የላኪው አገር ሥልጣን የተሰጠው አካል የፊርማ እና የማህተም ናሙና ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## ክፍል አራት

## ስለ የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ አሠራር

8. የሥሪት ሀገር መግለጫ የማድረግ ግዴታ፣

1) በዚህ መመሪያ አባሪ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ማናቸውም ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች እና/ወይም ማሸጊያዎቻቸው የተሰሩበትን አገር የሚያስረዳ መግለጫ በቀላሉ ሊፋቅ፣ ሊነሳ እና ሊለወጥ በማይችል መልኩ በእንግሊዘኛ ቋንቋ መጻፍ አለበት።

2) በዚህ መመሪያ አባሪ የተዘረዘሩት ዕቃዎች እና ከታች የተዘረዘሩት ዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ የማድረግ ግዴታ የለባቸውም።

(ሀ) ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ያገለገሉ ዕቃዎች፣

(ለ) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የፕሮጀክት ዕቃዎች ፣

(ሐ) አሮጌ ቁርጥራጭ እና ውዳቂ ዕቃዎች፣

(መ) ወደ ውጪ አገር የተላኩ የኢትዮጵያ ሥሪት ዕቃዎች ተመልሰው ሲመጡ፣

(ሠ) ዕቃ ታሽጎባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ፣ የያዙት ዕቃ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ የሚወገዱ የተለመዱ ማሸጊያዎችና መያዣዎች

(ረ) የወጪ ንግድ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች የሚያስገቧቸው ጥሬ ዕቃዎች፤

(ሰ) ከውጪ በሚያስገቡዋቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሥራ የሚሰሩ አምራች ድርጅቶች የሚያስመጡዋቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ በማሸጊያው ላይ የሥሪት አገር መግለጫ የማድረግ ግዴታ የለባቸውም።

9. <u>የሥሪት ሀገር ምልክት የሚደረግባቸው ማሸጊያዎች፤</u>

1) በተጣጣመ የሸቀጦች አሰያየም ሥርዓት አጠቃላይ የታሪፍ አተረጓጎም ደንብ 5 (ለ) መሰረት እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዲዛይን የተደረጉ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ማሸጊያዎችና መያዣዎች

2) የጠቅላላውን ዕቃ ዓይነተኛ ተግባር የሚወስኑ ከሆነ በአጠቃላይ የታሪፍ አተረጓጎም ደንብ 5 (ሀ) መሰረት እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ማሸጊያዎችና መያዣዎች፣

3) ለጉምሩክ ቀረጥ ሲባል ዕቃዉና ማሸጊያው ተለያይተው የሚታዩ ሲሆን፤ የማሸጊያ ማቴሪያሉ የሥሪት አገር ተለይቶ ሊወሰን ይችላል፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተቀመጠው ተግባራዊ በማይሆንበት ጊዜ የማሸጊያ ማቴሪያሉ የዕቃው አካል ተደርጎ ይወሰዳል፤ የዕቃው የሥሪት አገር ሲወሰንም በዚሁ ላይ በመመስረት ይሆናል፤

5) ዕቃዎችን ለማጓጓዝ እና በጊዜያዊነት ለማከማቸት የሚያገለግሉ ተመላሽ ኮንቴይነሮች ተመልሰው ከአገር ካልወጡ ለሥሪት አገር አወሳሰን በውስጣቸው ከታሸጉት ዕቃዎች የተለዩ ሆነው ይቆጠራሉ/ይወሰዳሉ፤

6) የአስመጪው አድራሻ የተጻፈባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማሸጊያዎችና መያዣዎች ላይ የዕቃዎቹ የሥሪት ሀገር ምልክት በማያሳስት ሁኔታ በማሸጊያዎችና መያዣዎች ላይ በግልጽ ተለይቶ መደረግ አለበት፡፡

10. <u>ተቀባይነት ያለው የሥሪት አገር አገላለጽ</u>

1) በዕቃው ወይም በዕቃው ማሸጊያ ላይ የሚደረገው የሥሪት አገር መግለጫ በተለመደው አገላለፅ መሆን የሚገባው ሲሆን የአገሮች አህፅሮተ ጽሁፎች የአገሩን ሥም በማያሳስት የሚያመለክቱት መሆን አለበት፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ቅፅላዊ ወይም የሥም ገላጭ መልክ ያላቸው የአገር ሥም አገላለፆች እንደ ትክክለኛ የሥሪት አገር አገላለፅ ተቀባይነት የሚኖራቸው ቅፅላዊ አገላለፁ የዕቃውን ዝርያ ለማመልከት ከሌሎች ቃላት ጋር የተቀመጠ ካልሆነ ነው፡፡

3) በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ የአገር ሥም ብቻ መጥቀስ ወይም ከአገሩ ሥም በፊት mode፣design ወይም style የማስገባት ዓይነት አገላለፅ፣ በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ አግባብ ያለው የሥሪት አገር መግለጫ እንዳልተደረገበት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

11. <u>የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ ተቀባይነት የሚያገኘው</u>

1) የሥሪት ሀገር መግለጫ በዕቃው ወይም በማሸጊያው ሳይጠፋ የመጨረሻ ገገር እጅ እስኪገባ ድረስ መቆየት የሚችል ከሆነ፤

2) የሥሪት ሀገር መግለጫው በወረቀት ስቲከሮች ላይ ተጽፎ በዕቃው ላይ የሚለጠፍ ከሆነ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍና ለክምችትና ለዕይታ በሚቆይበት ጊዜ እና ለመጨረሻ ገገር እጅ እስከሚደርስ ድረስ ሆን ተብሎ እንዳይላጥ ወይም እንዳይጠፋ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊቆይ በሚችል ሁኔታ የተለጠፈ ከሆነ፤

3) የሥሪት ሀገር መግለጫውን ለማድረግ ካርድ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ የሚታሰር እና ለመጨረሻ ተጠቃሚ እስከሚደርስ በዕቃው ላይ መቆየት የሚችል ከሆነ፤

4) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የመጨረሻ ገገር" ማለት

(ሀ) ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ መጨረሻ ላይ የሚገዛው ወይም የሚረከበው ሰው፤

(ለ) ከውጪ የገባው ዕቃ በምርት ግብዓትነት የሚያገለግል ከሆነና ዕቃው በምርት ሂደት መሰረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ያደረገ አምራች፤

(ሐ)ዕቃው ኢትዮጵያ የንግድ ስምምነት ካደረገችባቸው ሀገራት የመጣ ከሆነ እና በስምምነቶቹ የተቀመጠውን የሥሪት ሀገር መስፈርት የሚያሟላ አምራች ነው፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

12. <u>የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራር ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>

1) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት አስፈላጊው አሠራር እንዲዘረጋ በማድረግ በወጥነት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

2) በተለያየ ወቅት ኢትዮጵያ የምታደርጋቸውን የንግድ ስምምነቶችና የሥሪት አገር አወሳሰን ደንቦች በመቀበል ለተግባራዊነቱ ለሚመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና አካላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

3) በዋና መ/ቤት ሊሰጡ የሚገባቸው የሥሪት አገር ሰርተፊኬቶች ይሰጣል፡፡

4) በሁሉም የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ህጉንና አሠራሩ ወጥነትና በአግባቡ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

5) ከጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በጥናት የተመሠረተ ምላሽ ይሰጣል፡፡

6) ከተለያዩ አገራት በሥሪት አገር አሠራርና አወሳሰን ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

7) የመረጃ ጥናት (Statistics) በማደራጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

13. የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባር እና ኃላፊነት

1) በህጉ እና በተዘረጋው አሠራር መሠረት የሚቀርቡ ዕቃዎችን የሥሪት አገር በትክክል መቅረቡን ወይም መገለፁን የማጣራት፣ ተጨማሪ ማስረጃ የመጠየቅ፣ የመወሰን እና እርምጃ የመውሰድ ሥራዎችን በአግባቡ ይፈጽማሉ፡፡

2) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊሰጡ የሚገባቸውን የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች ይሰጣሉ፡፡

3) ከዋና መ/ቤት ወይም ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ተያያዥ ጥያቄዎች በጥናት የተመሠረተ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

4) የመረጃ ጥናት (Statistics) በማደራጀት ለዋና መ/ቤት ያስተላልፋሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## በዕቃዎች ሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰነድ ወይም አገላለጽ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ጥፋቶችና የሚወሰዱ ህጋዊ ዕርምጃዎች

14. የዕቃዎች ሥሪት አገር ጥፋቶችና የሚወሰዱ ህጋዊ ዕርምጃዎች፣

1) የሚከተሉት የዕቃዎች የሥሪት አገር አገላለጽ ጥፋቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፤

(ሀ) ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ወይም በሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰነድ ላይ ከተገለፀው የዕቃው ሥሪት አገር ባለሥልጣኑ በሚያደርገው የዕቃው አካላዊ ፍተሻ የሚገኘው የዕቃው የሥሪት አገር መግለጫ ጋር ልዩነት ያለው ከሆነ፤

(ለ) የቀረበው የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም ደጋፊ መረጃዎችና የሰነድ ማስረጃዎች የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ ከሆነ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገጉት ጥፋቶች ሲፈጸሙ ባለሥልጣኑ ያወጣው የአስተዳደራዊ መመሪያ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

15. <u>የሥሪት አገር ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 ከተቀመጠው አግባብ ውጪ በዕቃው እና በማሸጊያው ላይ የተገለፀው የሥሪት አገር መግለጫ የተለያየ ከሆነ በዕቃው ላይ ያለው መግለጫ ተወስዶ ከቀረቡት የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬትና ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማመሳከር ይወሰናል፤ ማሸጊያው ወይም መያዣው እንዲወገድ ይደረጋል።

2) በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ የዕቃው የሥሪት አገር መግለጫ ያልተገኘ ከሆነ እና ዕቃው በዚህ መመሪያ አባሪ ያልተካተተ ከሆነ በአዋጁ መሠረት ይስተናገዳል።

3) በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ የዕቃው የሥሪት አገር መግለጫ ያልተገኘ ከሆነ እና ዕቃው በአባሪ የተካተተ ከሆነ የሥሪት አገር ልዩነት እንደሌለው ተቆጥሮ የቀረበውን የሥሪት አገር ሰርተፊኬት እና ደጋፊ ሰነዶችን በማመሳከር ይወሰናል።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. <u>በልዩ ሁኔታ መስተንግዶ ስለመስጠት</u>

አስመጪው በጽሁፍ በሚያቀርበው አሳማኝ ምክንያት የሥሪት አገር የምስክር ወረቀት በወቅቱ ማቅረብ ካልቻለ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈፃፀምን ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል አራት መሠረት ደጋፊ ሰነዶችን አሟልቶ ለማቅረብ ስለሚሰጥ ዋስትና በተደነገገው አግባብነት ዋስትና በማቅረብ እንዲስተናገድ ይደረጋል።

17. <u>የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች የሚፈቱበት ሁኔታ</u>

የገቢ ዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን እና ምልክት አደራረግ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 107/2007 መሠረት ይታያል

18. <u>ስለተሻሩ መመሪያዎች</u>

1) የዕቃዎች ሥሪት አገር አወሳሰንን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 32/2001 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም አሠራር እና ልምድ በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

19. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ቀድሞ ሲሰራበት በነበረው መመሪያ ፍፃሜ ያገኛሉ።

20. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጠኑ ዋና ዳይሬክተር ከፀደቀበት ዘጠና የሥራ ቀናት በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት /2010 ዓ.ም

ሞገስ ባልቻ
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

## አባሪ

| | |
|---|---|
| 01.01 | በሕይወት ያሉ ፈረሶች ፣ አህያዎች ፣ በቅሎዎችና ሂኒዎች። |
| 01.02 | በሕይወት ያሉ የቀንድ ከብቶች። |
| 01.03 | በሕይወት ያሉ ዓሣዎች። |
| 01.04 | በሕይወት ያሉ በጎችና ፍየሎች |
| 01.05 | በሕይወት ያሉ ዶሮዎች፣ ይኸውም ማለት የ"ጋሉስ ዶመስቲክስ"፣ ዝርያ የሆኑ ዥግራዎች፣ ዳክዬዎች ዝይዎች፣ ተርኪዎችና ቆቆች። |
| 01.06 | ሌሎች በሕይወት ያሉ እንስሳት። |
| 03.01 | በሕይወት ያሉ ዓሣዎች። |
| 03.06 | ክረስታሺያንስ፣ በልባስ ውስጥ ቢሆኑም ባይሆኑም በሕይወት ያሉ ትኩስ በበረዶ የቀዘቀዘ፣ በማቀዝቀዣ የተጠበቀ፣ የደረቀ በጨው የተለወሰ ወይም በጨው ውሃ የተዘፈዘፈ፣ በጢስ የታጠነ ክረስታሺያንስ በልባስ ውስጥ ቢሆንም ባይሆንም የበሠለ ባይሆንም በጢስ ከመታጠኑ በፊት ወይንም በሚታጠንበት ሂደት ክረስቲሲያንስ በልባስ ውስጥ ያለ በእንፋሎት ወይም በውሃ የተቀቀለ በበረዶ የቀዘቀዘ ቢሆንም ባይሆንም ቢደርቅም ባይደርቅም በጨው ቢለወስም ወይም በጨው ውሃ ቢዘፈዘፍም ባይዘፈዘፍም፣ የተላመ የተፈጨና የተድቦለቦለ የክረስትሺያንስ ሥጋ፣ ለሰው ምግብነት ተስማሚ የሆነ። |
| 03.07 | ሞላሰክስ በልባስ ውስጥ ቢሆንም ባይሆንም በሕይወት ያለ፣ ትኩስ፣ በበረዶ የቀዘቀዘ፣ በማቀዝቀዣ የተጠበቀ የደረቀ በጨው የተለወሰ ወይም በጨው ውሃ የተዘፈዘፈ /ጢስ የነካው በልባስ ቢሆንም ባይሆንም ያልበሰለ ጢስ ከመደረጉ በፊት እና ጢስ በሚደረግበት ሂደት የተላመ የተፈጨ እና የተድቦለቦለ፣ ለሰው ምግብነት ተስማሚ የሆኑ። |
| 03.08 | አጥንት የሌላቸው በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ከክረስታሺያንስ እና ሞላሰስ ሌላ በሕይወት ያሉ፣ ትኩስ፣ በበረዶ የቀዘቀዘ በማቀዝቀዣ የተጠበቀ የደረቀ፣ በጨው የተለወሰ ወይም በጨው ውሃ ውስጥ የተዘፈዘፈ፣ ጢስ አጥንት የሌላቸው ውሃ ውስጥ የሚኖሩ ከክረስታሺያንስ እና ሞላሰክስ ሌላ ጢስ በማድረግ ሂደት የበሰሉ ወይም ያልበሰሉ፣ የተላመ የተፈጨ እና የተድቦለቦለ የዓሣ ሥጋ ለሰው ምግብነት ተስማሚ የሆነ። |
| 19.03 | ታፒኦካ እና ከስታርች የሚዘጋጅ እንደ ታፒኦካ የሚያገለግል፣ ፍላክስ፣ ግሬን፣ ፒርል፣ ንፊት የሆኑና ተመሳሳይ ዝግጅት ያላቸው። |
| 25.02 | ያልተጠበሱ የብረት ፓይራይትስ። |

| | |
|---|---|
| 25.04 | የተፈጥሮ ግራፋይት፡፡ |
| 25.05 | ማናቸውም ዓይነት የተፈጥሮ አሸዋዎች፣ የቀለሙ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ በምዕራፍ 26 ከሚመደቡት ሜታል-አዘል አሸዋዎች ሌላ፡፡ |
| 25.07 | ካኦሊንና ሌሎች የካኦሊን የሸክላ አፈሮች፣ የተቃጠሉ ቢሆንም ባይሆንም፡፡ |
| 25.08 | ሌሎች የሸክላ አፈሮች /በአንቀጽ 68.06 የሚመደቡ የናሩ የሸክላ አፈሮችን ሳይጨምር/፣ እንዱላሳይት፣ ኪያናይት እና ሲሊማናይት፣ የተቃጠሉ ቢሆኑም፣ ሙላይት፣ ሻሞቴ ወይም የዲናስ አፈሮች |
| 25.11 | የተፈጥሮ ቤሪየም ሶልት /ባራይትስ/፣ የተፈጥሮ ቤሪየም ካርቦኔት /ዊተራይት/፣ የተቃጠለ ቢሆንም ባይሆንም፤ በአንቀጽ 28.16 ከሚመደብ ቤሪየም ኦክሳይድ ሌላ፡፡ |
| 25.12 | የሲሊሽስ ፎሲል ሜልስ /ለምሳሌ ኬስልጉር፣ ትሪፖላይት እና ደያቶማይት /እናተመሳሳይ የሲሊሽስ አፈሮች፣ የተቃጠሉ ቢሆንም ባይሆኑም፣ ስፔሲፊክ ግራቪቴያቸው 1 ወይም ያነሰ መሆኑ የታወቀ፡፡ |
| 25.13 | ኤምሪ፣ የተፈጥሮ ኮረንደም፣ የተፈጥሮ ጋርኔትና ሌሎች የተፈጥሮ መሞረጃዎች |
| 25.17 | ጠጠር፣ ኮረት፣ የተፈጩ ወይም ደቃቅ ድንጋይ፣ ለኮንክሪት መሙሊያ፤ ለመንገድ ወይም ለሀዲድ ንጣፍ ወይም ለሌላ ለኮንክሪት መሙሊያ /ባላስት/ አገልግሎት ተዘውትረው የሚውሉ፣ ሺንግልና ፍሊንት፣ በሙቀት የተዘጋጁ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ የብረት-አር ዝቃጭ /ማክዳም/፣ የቀለጠ የብረታብረት ገፈት /ድሮስ/ ወይም ተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ውዳቂዎች፣ በአንቀጽ የመጀመሪያ ክፍል የተጠቀሱትን ነገሮች ቢጨመሩም ባይጨመሩም፣ ጥራን ወይም ሬንጅ የፈሰሰበት ማክዳም፣ በአንቀጽ 25.15 ወይም 25.16 የሚመደቡ የድንጋይ ኮረቶች፣ ስብርባሪዎችና ዱቄት፣ |
| 26.01 | የብረት አፈርና የብረት ክምችት በብዛት ያለበት አፈር፣ የተጠበሱ የብረት ፓይራይትስ፡፡ |
| 26.02 | የማንጋኒዝ አፈሮችና ኮንሰንትሬትስ፣ በደረቅ ክብደት ሲሰላ የማንጋኒዝ ይዞታቸው 20% ወይም የበለጠ የፌሮጂነስ ማንጋኒዝ አፈሮችና ኮንሰንትሬትስ ጭምር፡፡ |
| 26.03 | የመዳብ አፈሮችና መዳብ በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.04 | የኒኬል አፈሮችና ኒኬል በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.05 | የኮባልት አፈሮችና ኮባልት በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡ |
| 26.06 | የአልሙኒየም አፈሮች አልሙኒየም በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.07 | የእርሳስ አፈሮችና እርሳስ በብዘት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |

| | |
|---|---|
| 26.08 | የዚንክ አፈሮችና ዚንክ በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.09 | የቆርቆሮ አፈሮችን ቆርቆሮ በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.10 | የክሮሚየም አፈሮችና ክሮሚየም በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 16.11 | የተንግስተር አፈሮችና ተንግተን በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.12 | የዩራኒየም ወይም የቶሪየም አፈሮችና ማዕድኖች በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.13 | የሞሊብደነም አፈሮችና ሞሊብደነም በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 16.14 | የቲታኒየም አፈሮችና ቲታኒየም በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.15 | የኒዮቢየም፣ የታንታለም፣ የቫናዲየም ወይም የዚርኮኒየም አፈሮችና እነዚህ በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.16 | የከበሩ የብረታ ብረት አፈሮችና እነዚህ በብዛት የተከማቹባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.17 | ሌሎች የማዕድን አፈሮችና ማዕድን በብዛት የተከማቸባቸው አፈሮች፡፡ |
| 26.18 | ከብረት ወይም ከዓረብ ብረት ፋብሪካ የሚገኝ እንኳር የብረት አር /ስላግባንድ/፡፡ |
| 26.19 | የብረት አር፣ የቀለጠ ብረት ገፈት /ከእንኳር የብረት አር ሌላ/፣ከብረት ወይም ከዓረብ ፋብሪካ የሚገኙ ቅራፊዎችና ሌሎች ውዳቂዎች፡፡ |
| 26.20 | የብረት አር፣ አመድና ዝቃጭ /ከብረት ወይም ከዓረብ ፋብሪካ ከሚገኙት ሌላ/ ሜታል፣ አርሴኒክ ወይም የእነዚሁን ውሑዶች የያዙ፡፡ |
| 26.21 | ሌሎች የብረታ ብረት አርና አመድ፣ ሲዊድ አሽ /ኪልፕ/ ጭምር፣ በማቃጠል ከሚወገዱ ደረቅ ቆሻሻዎች የሚገኙ አመድና ዝቃጮች፡፡ |
| 27.01 | የድንጋይ ከሰል፣ ብራክትስ፣ አቮይድስና እነዚህን የመሳሰሉ |
| 27.02 | ሊግናይት፣ ግግር ቢሆንም ባይሆንም፣ ከጄት በስተቀር፡፡ |
| 27.03 | ፒት /ፒት ሊትር ጭር/፣ ግግር ቢሆንም ባይሆንም፡፡ |
| 27.04 | ኮክ እና ከፊል -ኮክ ከድንጋይ ከሰል፣ ከሊግናይት ወይም ከፒት የተገኙ፣ ግግር ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ሪቶርት ካርቦን፡፡ |
| 27.05 | ቅጥራን፣ ከድንጋይ ከሰል፣ ከሊግናይት እና ከሌሎች የማዕድን ቅጥራኖች የተነጠረ፣ ውሃ የተወገደለት ወይም በከፊል የተነጠረ ቢሆንም ባይሆንም እንደገና የተዘጋጀ ቅጥራን ጭምር፡፡ |
| 27.06 | ዘይቶችና ሌሎች ውጤቶች፣ በከፍተኛ የሙቀት ኃይል የድንጋይ ከሰል ቅጥራንን በማንጠር |

| | |
|---|---|
| | የሚገኙ፣ በክብደት መዓዛ ያላቸው ቅንብሮች መዓዛ ከሌላቸው ቅንብሮች በልጠው የሚገኙባቸው ተመሳሳይ ውጤቶች፡፡ |
| 27.08 | ፒችና ፒች ኮክ፣ ከድንጋይ ከሰል ቅጥራን ወይም ከሌሎች የማዕድን ቅጥራኖች የሚገኙ፡፡ |
| 27.09 | የፔትሮሊየም ዘይቶችና ቅጥራንነት ካላቸው ማዕድኖች የሚገኙ ዘይቶች፣ ያልተነጠሩ፡፡ |
| 27.10 | የፔትሮሊየም ዘይቶችና ቅጥራንነት ካላቸው ማዕድኖች የሚገኙ ዘይቶች፣ ካልተጣሩ ዘይቶች ሌላ፣ በሌላ ስፍራ ያልተገለፁ ወይም ያልተመለከቱ ዝግጅቶች፣ በክብደት 70% ወይም የበለጠ የፔትሮሊየም ዘይቶችን ወይም ቅጥራንነት ካለቸው ማዕድኖች የተገኙ ዘይቶችን የያዙ፣ እነዚህ ዘይቶች የዝግጅቱ መሠረታዊ ቅንብሮች ሆነው ሲገኙ፣ ውዳቂ ዘይቶች፡፡ |
| 27.11 | የፔትሮሊየም ጋዞች ሌሎች ጋዝ የሆኑ ሀይድሮካርቦንስ፡፡ |
| 27.12 | ፔትሮሊየም ጄሊ፣ የፓራፊን ሰም፣ የማይክሮካሪስ ታላይን ፔትሮሊየም ሰም፣ ስላክ ሰም፣ ኦዞከራይት፣ ሊግናይት ሰም፣ ፒት ሰም፣ ሌሎች የማዕድን ሰሞች እና በሲንቴሲስ ወይም በሌላ አሠራር የሚገኙ ሌሎች ተመሳሳይ ውጤቶች፣ የቀለሙ ቢሆንም ባይሆንም፡፡ |
| 27.13 | ፔትሮሊየም ኮክ፣ የፔትሮሊየም ቅጥራንና ሎሎች ከፔትሮሊየም ዘይቶች ወይም ቅጥራንነት ካላቸው ማዕድን ዘይቶች የሚገኙ ዝቃጮች፡፡ |
| 27.14 | የተፈጥሮ ቅጥራንና አስፋልት፣ ቅጥራን ያለው ወይም ዘይት የሚወጣው ሼል እና ቅጥራን ያለው አሸዋ፣ አስፋልታይትስና አስፋልትነት ያለው ድንጋይ፡፡ |
| 27.15 | በተፈጥሮ አስፋልት፣ በተፈጥሮ ቅጥራን፣ በፔትሮሊየም ቅጥራን፣ በማዕድን ቅጥራን ወይም በማዕድን ቅጥራን ፒች ላይ የተመሠረተ ቅጥራንነት ያለቸው ድብልቆች /ለምሳሌ፣ የቅጥራን ማጣበቂያ ኮት- ባክስ/፡፡ |
| 27.16 | የኤሌክትሪክ ኃይል፡፡ |
| 30.02 | የሰው ደም፣ ለሕክምና፣ ለበሽታ መከላከያ ወይም ለምርመራ አገልግሎት የሚውል የእንስሳ ደም፣ አንቲሴራ እና ሌሎች የደም ክፍልፋዮች እና ኢሚውኖሎጂካል ውጤቶች፣ የተሻሻሉ ወይም በባዮቴክኖሎጂካል ዘዴ የተገኙ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ክትባቶች፣ ቶክሲኖች፣ የተራቡ ረቂቅ ተህዋስያን /እርሾን ሣይጨምር/ እና ተመሣሣይ ውጤቶች፡፡ |
| 39.15 | የፕላስቲክ ውዳቂዎች፣ ቁርጥራጮችና ልቃሚዎች፡፡ |
| 40.01 | የተፈጥሮ ላስቲክ፣ ባላታ፣ ጉታ-ፔርካ፣ ጓዮል፣ ቹክልና የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሙጫዎች በፕራይመሪ ፎርም ወይም በጥፍጥፍ፣ በዝርግ፣ ወይም በጥቅል መልክ የሚገኙ፡፡ |

Federal Democratic Republic of Ethiopia

| | |
|---|---|
| 40.02 | ሲንተቲክ ላስቲክና ከዘይቶች የተገኘ ፋክቲስ፣ በፕራይመሪ ፎርም ወይም በጥፍጥፍ፣ በገርግ ወይም በጥብጣብ መልክ የሚገኙ፣ የአንቀጽ 40.01 እና የዚሁ አንቀጽ ማናቸውም ውጤቶች ድብልቆች፣ በፕራይመሪ ፎርም ወይም በጥፍጥፍ፣ በገርግ ወይም በጥብጣብ መልክ የሚገኙ። |
| 40.03 | በፕራይመሪ ፎርም ወይም በጥፍጥፍ፣ በገርግ ወይም በጥብጣብ መልክ በሚገኝ ተለቃቅሞ የተሠራ ላስቲክ። |
| 40.04 | የላስቲክ ውዳቂ፣ ፍቅፋቂና ቁርጥራጭ /ከጠንካራ ላስቲክ በቀር/ እና ከእነዚህ የሚገኙ ዱቄቶችና ጠጠሮች። |
| 40.05 | ውሑድ ላስቲክ፣ ቮልካናይዝድ ያልሆነ በፕራይመሪ ፎርም በጥፍጥፍ፣ በዝርግ ወይም በጥብጣብ መልክ የሚገኙ። |
| 41.01 | የቀንድ (የጎሽ ጭምር) ወይም የጋማ ከብቶች ያልተለፉ ቆዳዎችና ሌጦዎች /እርጥብ፣ ወይም በጨው የታጀሉ፣ የደረቁ፣ በኖራ የታጀሉ፣ በመድኃኒት የተጠበቁ ወይም በሌላ አኳኋን የተጠበቁ፣ ነገር ግን ያልተለፉ፣ ወደ ብራናነት ያልተለወጡ ወይም ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገባቸው /ፀጉር የተወገደለት ወይም የቆዳው ውስጥና የውጭው ንብርብር የተለያየ ቢሆንም ባይሆንም። |
| 41.02 | የበግ ወይም የበግ ጠቦቶች ያልተለፉ ሌጦዎች /እርጥብ፣ ወይም በጨው የታጀሉ፣ የደረቁ፣ በኖራ የታጀሉ፣ የታጀሉ ወይም በሌላ አኳኋን የተጠበቁ፣ ነገር ግን ያልተለፉ፣ ወደ ብራናነት ያልተለወጡ ወይም ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገላቸው/፣ ከእነሱፋቸው ወይም የቆዳው የውስጥና የውጭ ንብርብር የተለያየ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ በዚህ ምዕራፍ መግለጫ 1/ሐ/ እንደማይመደቡ ከተገለጹት በቀር። |
| 41.03 | ሌሎች ያልተለፉ ቆዳዎችና ሌጦዎች /እርጥብ፣ ወይም በጨው የተጠበቁ፣ የደረቁ፣ በኖራ የተጠበቁ፣ የታጀሉ ወይም በሌላ አኳኋን የተጠበቁ፣ ነገር ግን ያልተለፉ፣ ወደ ብራናነት ያልተለወጡ ወይም ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገላቸው/፣ የተሸለቱ ወይም የቆዳው የውስጥና የውጭ ንብርብር የተለያየ ቢሆንም ባይሆንም፣ በዚህ ምዕራፍ በመግለጫ 1/ለ/ ወይም 1/ሐ/ እንደማይመደቡ ከተገለጹት በቀር። |
| 41.04 | የተለፉ ወይም ተለፍተው የደረቁ የቀንድ ከብት /የጎሽ ጭምር/ ወይም የጋማ ከብት ቆዳና |

| | |
|---|---|
| | ሌጦዎች፣ ፀጉር ሳይኖራቸው፣ የቆዳው ንብርብሮች ቢለያዩም ባይለያዩም፣ ነገር ግን ከዚህ አልፎ ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገላቸው። |
| 41.05 | የተለፉ ወይም ተለፍተው የደረቁ የበግ ወይም የበግ ጠቦት ሌጦዎች፣ ሱፍ ሳይኖራቸው፣ የቆዳው ንብርብሮች ቢለያዩም ባይለያዩም፣ ነገር ግን ከዚህ አልፎ ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገላቸው። |
| 41.06 | የሌሎች እንስሳት የተለፉ ወይም ተለፍተው የደረቁ ቆዳና ሌጦዎች፣ ሱፍ ወይም ፀጉር ሳይኖራቸው፣ የቆዳው የውስጥና የውጭ ንብርብር የተለያየ ቢሆንም ባይሆንም፣ ነገር ግን ከዚህ አልፎ ተጨማሪ ዝግጅት ያልተደረገላቸው። |
| 43.01 | ያልተለፉ ፈርስኪን ለፈር ሥራ አገልግሎት የሚውሉ ጭንቅላት፣ ጅራት፣ መዳፍና ሌሎች ቁርጥራጮች ወይም ቅንጥብጣቢዎች ጭምር /በአንቀጽ 41.01፣ 41.02 ወይም 41.03 ከሚመደቡት ያልተለፉ ቆዳዎችና ሌጦዎች ሌላ/። |
| 43.02 | የተለፉ ወይም የተዘጋጀ ፈርስኪን /ጭንቅላት፣ ጅራቶች፣ መዳፎች እና ቁርጥራጮች ወይም ቅንጥብጣቢዎች ጭምር/፣ ያልተገጣጠሙ፣ ወይም የተገጣጠሙ፣ ሌሎች ማቴሪያሎች ሳይጨመሩባቸው /በአንቀጽ 43.03 ከሚመደቡት ሌላ። |
| 44.01 | በግንድ፣ በፍልጥ፣ በጨራሮ፣ በጨፈቃ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኝ የማገዶ እንጨት፣ ቁርጥራጭ ወይም ቅርጥፍጣፊ እንጨት የእንጨት ብናኝና ውዳቂ እና ስብርባሪ፣ በግንድ በብሪኬት፤ በድቡልቡል ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተጣበቀ ቢሆንም ባይሆንም። |
| 44.02 | የእንጨት ከሠል (የሼል ወይም የነት ከሠል ጭምር)፣ የተጣበቀ ቢሆንም ባይሆንም። |
| 44.03 | ያልተሠራ ግንድ፣ ቅርፊቱ ወይም ሳፕውድ የተላጠ ቢሆንም ባይሆንም፣ በመጠኑ በአራት ማዕዘን የተጠበቀ። |
| 44.04 | የበርሜል ግድግዳ መሥሪያ እንጨት፣ የተሰነጠቁ ምሶሶዎች፣ ለመሠረትነት የሚውሉ ከባድ ግንዶች፣ የእንጨት ችካሎችና የወሰን ማካለያዎች፣ የሾሉ ነገር ግን በቁመት ያልተመገዙ፣ የእንጨት ዘንጎች፣ በመጠኑ የተስተካከሉ ነገር ግን ያልተቆለመሙ፣ ያልጎበጡ ወይም በሌላ አኳኋን ያልተዘጋጁ፣ ከዘራዎች፣ ጃንጥላዎች፣ የእጅ መሣሪያ እጀታዎች ወይም የመሳሰሉት ለመሥሪያ ተስማሚ የሆኑ፣ ቺፕ ውድ እና የመሳሰሉት። |
| 44.05 | የእንጨት ሱፍ፤ የእንጨት ዱቄት |

| | |
|---|---|
| 44.07 | በርዝመቱ የተመገዘ ወይም የተቆረጠ እንጨት፣ በስሱ የተሰነጠቀ ወይም የተላጠ፣ የተላገ ወይም በብርጭቆ ወረቀት የለሰለሰ ወይም ጫፍ ለጫፍ የተገጣጠመ ቢሆንም ባይሆንም፤ ከ6 ሚ.ሜ የበለጠ ውፍረት ያለው:: |
| 44.08 | ለቪኒር /ላሚኔትድ እንጨት በስሱ በመመገዝ የሚገኙ ጭምር/፣ ለንብርብር እንጨት ወይም ለሌላ ተመሣሣይ ላሚኔትድ እንጨት እና ለሌሎች እንጨቶች የሚሆኑ ዝርጎች፣ በርዝመት የተመገዙ፣ በስሱ የተመገዙ ወይም የተላጡ፣ የተላጉ፣ በብርጭቆ ወረቀት የለሰለሱ፣ ጫፋቸውን በማጣበቅ የተያያዙ ወይም የተገጣጠሙ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ከ6 ሚ.ሜ ያልበለጠ ውፍረት ያላቸው:: |
| 45.01 | የተፈጥሮ ቡሽ፣ ያልተዘጋጀ /ያልተሠራ/ ወይም በመጠኑ የተዘጋጀ፣ ውዳቂ ቡሽ፣ ያልተሰባበረ፣ ስቃቅ ወይም የተፈጨ ቡሽ:: |
| 45.02 | የተፈጥሮ ቡሽ፣ ቅርፊት የተወገደለት ወይም በመጠኑ የስኩዌርነት ቅርጽ የተሰጠው፣ ወይም የሬክታንግል/ ስኩዌር ጭምር/ ቅርጽ ባላቸው ጉማጆች፣ ጥፍጥፎች፣ ዝርጎች ወይም ጥብጣቦች የተዘጋጀ፣ /ለቡሽና ለውታፎች የሚያገለግሉ ሹል ብላንኮች ጭምር/:: |
| 47.06 | ከልቅምቃሚ /ውዳቂና ቁርጥራጭ/ ወረቀት ወይም ካርቶን ፋይበር የተገኘ ፐልፕ ወይም ከሌሎች ሴሉሎስ ካላቸው ማቴሪያሎች ፋይበር የተገኘ ፐልፕ:: |
| 47.07 | ልቅምቃሚ /ውዳቂና ቁርጥራጭ/ ወረቀት ወይም ካርቶን:: |
| 63.09 | ያገለገሉ ልብሶች እና ሌሎች ያገለገሉ ዕቃዎች:: |
| 63.10 | ያገለገሉ ወይም አዲስ ቁርጥራጭ ጨርቆች፣ ቁርጥራጭ ሲባጎ፣ ቀጭን እና ወፍራም ገመድ እና ኬብሎች እና የሲባጎ፣ የቀጭን እና የወፍራም ገመድ ወይም የኬብል አሮጌ ዕቃዎች፤ ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ:: |
| 70.01 | ከሌት፣ እና ሌሎች የብርጭቆ ውዳቂና ስብርባሪ፣ የብርጭቆ ክምችት:: |
| 72.01 | ጠገራ ብረት እና የስፔገሊዘን ጠገራዎች፣ ብሎኮች ወይም ሌሎች በጥሬ መልክ ያሉ :: |
| 72.02 | ፌሮ-አሎይስ :: |
| 72.03 | ከብረት አፈር እና ከስፖንጅ ፌሮስ ውጤቶች በቀጥታ ተለይተው የወጡ የፌሮስ ውጤቶች፣ ቅርጽ በሌለው ክምችት፣ወይም ሞላላና ተመሣሣይ ቅርጾች የሚገኙ፣ በክብደት 99.94% የሆነ ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ያለው ብረት፣ ቅርጽ በሌለው ክምችት ፣ በሞላላናተመሣሣይ ቅርጾች የሚገኙ:: |
| 72.04 | የፌሮስ ውዳቂና ቁርጥራጭ ፣ እንደገና የሚቀልጡ የብረት ወይም የአረብ ብረት የኢንጎት |

Addis Ababa, Ethiopia

| | |
|---|---|
| | ቁርጥራጮች። |
| 72.05 | የጠገራ ብረት፣ የስፒግሊዘን፣ የብረትና የአረብ ብረት ጠጠሮችና ዱቄቶች። |
| 72.06 | II. ብረት እና አሎይ ያልሆነ ዓረብ ብረት ቀልጦ ቅርጽ የወጣለት /በኢንጎት/ ወይም በሌሎች ጥሬ መልክ የሚገኝ ብረት እና አሎይ ያልሆነ የአረብ ብረት በአንቀጽ 72.03 ከሚመደቡት ብረት በስተቀር/። |
| 72.07 | ብረት ወይም አሎይ ያልሆነ የአረብ ብረት ሆነው በከፊል የተሠሩ ውጤቶች። |
| 72.27 | ወፍራምና ቀጭን ዘንጎች፣ በሙቀት የተዳመጡ፣ በስርአት ያልተጠመጠሙ ከሌሎች አሎይ ዓረብ ብረቶች የተሠሩ። |
| 72.28 | ከሌሎች አሎይ ዓረብ ብረት የተሠሩ ሽቦዎች። |
| 73.20 | ሞላዎች እና የባሌስትራ ቅጠል ከብረት ወይም ከዐረብ በረት የተሠሩ። |
| 75.01 | የኒኬል ድፍድፍ፣ የኒኬል ኦክሣይድ ሴንትሮስ እና ሌሎች ስራቸው ያላለቀላቸው የኒኬል ሜታሎጂ ውጤቶች። |
| 78.04 | ከሊድ የተሠሩ ጥፍጥፎች፣ ዝርጎች፣ ጥብጣቦች እና ቅጠሎች፣ የሊድ ዱቄቶችና ሽርክቶች። |
| 79.04 | ከዚንክ የተሠሩ ወፍራም እና ቀጭን ዘንጎች፣ ፕሮፋይልስ እና ሽቦዎች። |
| 79.05 | የዚንክ ጥፍጥፎች፣ ዝርጎች፣ ጥብጣቦች እና ቅጠሎች ። |
| 80.02 | የቆርቆሮ ውዳቂ እና ቁርጥራጭ |
| 80.03 | ከቆረቆሮ የተሠሩ ወፍራምና ቀጭን ዘንጎች፣ ፕሮፋይልስ እና ሽቦዎች። |
| 81.01 | ተንግስተን /ዎልፍራም/ እና ከዚህ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ውዳቂና ቁርጥራጭ ጭምር |
| 81.02 | ሞሊብደነም እና ከነዚህ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ውዳቂና ቁርጥራጭ ጭምር ። |
| 81.03 | ታንታለም እና ከነዚህ የተሠሩ ዕቃዎችን፣ ውዳቂና ቁርጥራጭ ጭምር። |
| 81.04 | ማግኒዚየም እና ከነዚህ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ውዳቂና ቁርጥራጭ ጭምር። |
| 81.05 | የኮቦልት ድፍድፍና እና በኮባልት የሚታስርጂ ስራ ሂደት የተገኙ ስራዊ ያላለቀላቸው ሌሎች ውጤቶች፣ ኮቦልትና ከነዚህ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ውዳቂና ቁርጥራጭ፣ ጭምር ። |

ቅ/ጽ/ቤቶች

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ለአዳማ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

አዳማ

ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ሞጆ

ለሐዋሳ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ሐዋሳ

ለባህር ዳር ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ባህር ዳር

ለመቀሌ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

መቀሌ

ለድሬደዋ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ድሬደዋ

ለጅማ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ጅማ

ለጅጅጋ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ጅጅጋ

ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ጋላፊ

ለሚሌ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ሚሌ

ለኮምቦልቻ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ኮምቦልቻ

ለሞያሌ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት

ሞያሌ